# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## በመስቀል ሳምንት ውስጥ ሁለተኛ እሑድ ቢውል

በመስቀል ሳምንት ውስጥ ሁለተኛ እሑድ ቢውል የሚዘመረው መዝሙር፣ የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደ መጀመሪያው እሑድ በክብረ መስቀል ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

### የዕለቱ ምስባክ

ወአጽንእ እግዚኦ ለዝንቱ ዘሠራዕከ ለነ
ውስተ ጽርሕከ ዘኢየሩሳሌም
ለከ ያመጽኡ ነገሥት አምኃ

አቤቱ ይህን ለእኛ የሠራኸውን አጽናው
ከኢየሩሳሌም ስላለው መቅደስህ
ነገሥታት እጅ መንሻቸውን ለአንተ ያመጣሉ

መዝ ፷፯፥፳፰-፳፱

ወንጌል፥ ሉቃስ ፱፥፲፰-፳፰
ቅዳሴ፥ ዘእግዚእነ (ነአኵተከ) የጌታ ቅዳሴ

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

መስቀልከ እግዚኦ ተሰብሐ (አቤቱ መስቀልህ ተመሰገነ)
ወይም
ወቦ ዘይቤ ዝንቱ መስቀል ረድኤት ለእለ ነአምን
(ይህ መስቀል ለምናምን ሰዎች ረድኤታችን ነው)
ከሚሉት ሁለት መዝሙራት አንዱ ይዘመራል።

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፪፥፩-፲፪ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፪፥፳-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፬፥፲፱-፴፩ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### የዕለቱ ትምህርት

## ነገረ መስቀል

ነገረ መስቀል ሲዘከር፣ መስቀል የሚለው ቃል ሲነገርም ሆነ ሲሰማ በክርስቲያኖች ልብ ውስጥ ልዩ መንፈስ ይፈጥራል። መስቀል በእርሱ ላይ የተሰቀለውን እግዚአ-ኃይላት ክርስቶስን ያሳስባልና፤ የእሾህ አክሊል ደፍቶ፣ ጎኑን በጦር ተወግቶ፣ በብዙ መከራና ስቃይ በቀራንዮ የዋለውንም ጌታ በውስጣችን ይስላልና።

የሲዖል መሠረት የተናወጠበት፣ ሰውና እግዚአብሔርን ለዘመናት ለያይቷቸው የነበረው የጠብ ግርግዳ የተናደበት፣ ሞት ድል የሆነበት፣ የትንሣኤ መንገድ የተከፈተበት ልዩ መንፈሳዊ መሳሪያ መስቀል ነው።

ስለዚህ መስቀል ለምዕመናን የነፃነታቸው፣ የእርቃቸውና የሰላማቸው ምልክት በመሆኑ ለመስቀል ልዩ ክብርን ይሰጣሉ፣ ይሰግዱለታልም። ማንኛውም ተግባር ጸሎትን፣ ምግብን፣ ጉዞን ከመጀመር በፊትና ከኋላ በትእምርተ መስቀል ያማትባሉ። በፈተና፣ በሐዘንና ክፉ ሃሳብ በሕሊናቸው በተፈጠረ ጊዜ ሁሉ ያማትባሉ። በከበረ ደሙ መስቀሉን የቀደሰ ጌታቸው በኃይለ መስቀሉ ሁሉን ሊያደርግላቸው እንደሚችል በመታመን ይህን ያደርጋሉ።

እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን ከፈጠረበት ጥበብ በሚበልጥ ጥበብ ዓለምን ሁሉ ያዳነበት ከጥበብ ሁሉ በላይ የሆነ ጥበብ ይህ መስቀል ነው። ለዚህ ነው ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን «መስቀል መልዕልተ ኵሉ ነገር - መስቀል ከሁሉ ነገር በላይ ነው» ያሉት። ይህ የመስቀል ነገር አምላክን ሰው እስከ መሆንና እስከ መሪር ሞት ያደረሰውን ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ከማንከር በስተቀር ሊመረመርና ድርሰ-ነገሩ ሊስተዋል የማይቻል ረቂቅ ነው። በመሆኑም ነገረ መስቀሉ ለአንዳንዶች ፈተና ለሌሎችም ስንፍና ሆኖባቸዋል። ለሚያምኑ ምዕመናን ግን ከፈተና እንደ ወርቅ ነጥረው የሚወጡበት ነው።

መስቀል ሕይወትን ሊያጠፉ በተነሱ ጠላቶች ቢዘጋጅም ቅሉ በእርሱ አዲስ ዘለዓለማዊ ሕይወት ተዘጋጅቷል። በእውነት ጠላቶች እውነትን ለማጥፋት ቢዘጋጁም በእርሱ ለዓለም እውነት

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## በመስቀል ሳምንት ውስጥ ሁለተኛ እሑድ ቢውል

ተሰብኳል። አይሁድ ሰዎችንና ክርስቶስን ለማራራቅ የምዕመናን ራስ ክርስቶስን በመስቀል ቢሰቅሉትም በመስቀል ያፈሰሰው ክቡር የሚሆን ደሙ ዓለሙን ሁሉ ወደ እርሱ አቅርቧል። «እምከመ ተለዓልኩ እምድር አስህብ ኩሎ ኀቤየ - ከምድር ብቅ ከሰማይ ዝቅ ብዬ በተሰቀልኩ ጊዜ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ። በማለት ጌታችን ራሱ እንደገለጸው በመስቀሉ የሰውን ልጅ ወደ ራሱ አቅርቦታል። በተመሳሳይ መንፈስ «ዘበመስቀልከ አቅረብከነ ኀበ አቡከ - በመስቀልህ በፈጸምከው መስዋዕትነት ወደ ባሕርይ አባትህ ወደ እግዚአብሔር አቀረብከን፤ ከእርሱም እርቅንና ሰላምን እንድናገኝ አደረከን» እንዳለ ሊቁ።



የነቢያት ሁሉ ዋናው የትንቢታቸው ዓላማ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ክርስቶስ በህማመ መስቀል፣ በሞተ መስቀል ዓለምን ሁሉ እንደሚያድን መግለጽ ነበር። የሐዋርያትም ስብከት «ንህነሰ ንስብክ ክርስቶስሃ ዘተሰቅለ - እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን» የሚል ነበር (፩ኛ ቆሮ ፩፤፳፫)። ለዚህ ነው ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ መስቀል ኃይል ሲናገር «መስቀል የክርስቲያኖች ተስፋ ነው፤ መስቀል የሙታን ትንሣኤ ነው፤ መስቀል የእውራን መሪ ነው፤ መስቀል ተስፋ ቅቡጻን ነው» ካለ በኋላ «መስቀል ትንቢተ ነቢያት ነው፤ መስቀል ስብከተ ሐዋርያት ነው፤ መስቀል ክብረ ሰማዕታት ነው፤ መስቀል የጻድቃን ሞገስ ነው፤ መስቀል የመነኮሳት ጽሙና ነው፤ መስቀል የደናግል ንጽሕና ነው፤ መስቀል የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው፤ መስቀል የዓለም መረጋጋት ሰላምም ነው።» ያለው (ግብረ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅጽ ፪)።

ይኸው ሊቅ በሌላ ክፍል «ክፉ መንፈስ የተመታበትንና የቆሰለበትን ሰይፍ ካየ ወደ ባለ ሰይፉ ሊቀርብ አይችልም ... ስለዚህ በቤታችን፣ በግርግዳችን፣ በበራችን፣ በግንባራችን፣ በደረታችን፣ በጣታችንና በክንዳችን የመስቀል ምልክት ይኑረን። ምክንያቱም መስቀሉ ድላችን ነው፤ ከተሰጡን በረከቶች ሁሉ ታላቁ በረከት ነው ... የቤተ ክርስቲያን ጌጥ ነው፤ በመሆኑም መስቀሉን በአእምሮአችሁ እንደ ማህተም አትሙት፤» (ግብረ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅጽ ፯) በማለት ይመሰክራል።

ይህን ሁሉ በማሰብ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ መስቀሉ የራሷ የክርስቶስ አካል በቀኖት የተቸነከረበት፣ ደሙ የነጠበበት፣ ታላቅም ኃይል የተፈጸመበት ስለሆነ ትስመዋለች፣ ታከብረዋለች። በዓመት ሁለት ጊዜ (በመጋቢት ፲ እና በመስከረም ፲፯) ልዩ ሥነ-በዓል አድርጋ ብታከብረውም በየዕለቱና በየሰዓቱ ነገረ መስቀሉን ታስባለች። ነገረ መስቀሉ የማይዘከርበት፣ የመስቀል ክብሩ የማይገለጥበት ሥርዓተ አምልኮት፣ ሥርዓተ ማኅሌትና ሥርዓተ ጸሎትም የላትም፤ በመስቀል የሰው ልጅ የበደል ካሳ አግኝቶበታልና።

ምንጭ፥
*ፈለገ ጥበብ መጽሔት መስከረም ፲፱፻፺፬ ዓ.ም.*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።